በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

Federal Democratic Republic of Ethiopia
CIVIL SERVICE COMMISSION

ቁጥር/Ref.No. ኔ/አ/ኮ/ጠ/ጠ0/6/13/151

ቀን/ Date 05 የካቲት 2013

ለጤና ሚኒስቴር

አዲስ አበባ

በመንግሥት ጤና ተቋማት የሚሠሩ የጤና ባለሙያዎች የቅጥር እና የደረጃ እድገት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 4/2013 ታህሣስ 23 ቀን 2013 ዓ.ም በቁጥር ሲ/ሰ/ኮ30/ጠ10/6/13 በተጻፈ ደብዳቤ የተላከ መሆኑ ይታወቃል።

መመሪያውን ለክልል በጤና ቢሮ፣ ለጤና ተጠሪ ተቋማት እና ለዩኒቨርስቲ ተወካዮች ለማስተዋወቅ ጥር 7 እና 8 ቀን 2013 ዓ.ም በጤና ሚኒስቴር አስተባባሪነት በተካሄደው ስብሰባ ላይ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ተነስተው ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል።

በእለቱ ከተነሱ ጥያቄዎች መካከል በስብሰባው ያልተሳተፉ የሰው ሀብት ባለሙያዎች ግንዛቤ ቢያገኙበት መመሪያው ሲተገበር አንድ ወጥ አሠራር ለማስፈን ይጠቅማሉ የተባሉትን በመምረጥ በጤና ሚኒስቴር እና ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተወካዮች የተዘጋጀውን ማብራሪያ ከዚህ ጋር አያይዘን መላካችንን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

ዶ/ር ጀማነህ አመነሸዋ
የተቋማዊ አደ/የሥራ ምዘናና የሰው ሃ/ል/ዳይ/ጀነራል

ግልባጭ
- ዝርዝራቸው ከዚህ ጋር ተያይዞ ለሚገኝ ተቋማት ባሉበት
- ለአደረጃጀት ሥራ ምዘናና ክፍያ ጥናት ዳይሬክቶሬት ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

ስልክ /Tel: +251 115 54 96 66/67
ፋክስ /Fax: +251 115549707
Email:- ethiocsc@gmail.com
Website:- www. csc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa Ethiopia

## በመንግሥት የጤና ተቋማት የሚሠሩ የጤና ባለሙያዎች የቅጥር እና የደረጃ እድገት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 4/2013ን ለማስተዋወቅ በተዘጋጀ መድረክ የተነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ

### 1 ቅጥር

1. ከሌላ መ/ቤት አገልግሎት ኖሮት ዝቅ ብሎ የተቀጠረ ሠራተኛ ወዲያውኑ ወደ ነበረበት ደረጃ ላይ ማሻሻያ አድርጎ መመደብ ይቻላል?

   ➢ በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተቀጠሮ በጤና ባለሙያነት ያገለገለ ከሆነ የሙከራ ቅጥር ጊዜውን ሲያጠናቅቅ ብቻ ቀድሞ ደርሶበት ወደነበረው ደረጃ ከፍ ተደርጎ ደመወዙ እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡ /መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 5.2 ይመልከቱ/

2. የሌላ ተቋም ልምድ የተያዘለት ሠራተኛ ሙከራ ቅጥር ላይ እያለ የደረጃ ዕድገት ማግኛ ጊዜው ቢደርስ እንዴት ይደረጋል?

   ➢ የሙከራ ጊዜውን ያልጨረሰ ሠራተኛ ደረጃ ዕድገት ማግኘት አይችልም፡፡ ሆኖም የሙከራ ጊዜውን ከመጨረሱ በፊት የሶስት ዓመት መቆያ ጊዜው ቢደርስ ሠራተኛው ቋሚ ከሆነ በኋላ በመመሪያው አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 10.1 መሠረት የደረጃ እድገቱን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

## 2 መደበኛ የደመወዝ ጭማሪ

1. መደበኛ የደመወዝ ጭማሪ ምንድነው? ለማን ነው የሚሰጠው? ከደረጃ እድገት የሚለይ ከሆነ ቢብራራ?

   ➢ መደበኛ የደመወዝ ጭማሪ የጤና ባለሙያን ጨምሮ ለማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በተመደበበት የሥራ መደብና ደረጃ ላይ ቢያንስ ሁለት ዓመት ሲያገለግል ያስመዘገበውን መካከለኛና በላይ የውጤት ተኮር የምዘና ውጤትን መሠረት በማድረግ ላለፈ ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥ የአንድ እርከን የደመወዝ ጭማሪ ሲሆን፣ የደረጃ እድገት አንድ ሠራተኛ ካለበት ዝቅ ያለ የሥራ መደብና ደረጃ የተቀመጡ መስፈርቶችን በማሟላት ከፍ ወዳለ የሥራ ተዋረድ የሚሸጋገርበት የምልመላና መረጣ የአሠራር ስልት ነው፡፡

2. በጥር 2013 የደረጃ ዕድገት ያገኘ የጤና ባለሙያ ለመደበኛ የደመወዝ ጭማሪ ልምድ ከመቼ ጀምሮ ነው የሚቆጠርላቸው?

   ➢ የመንግስት ሠራተኞች መደበኛ የደመወዝ ጭማሪ ተግባራዊ የሚሆነው ወደፊት ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በሚወጣ ዝርዝር መመሪያ መሠረት ስለሆነ ከዚያ በፊት ምንም ዓይነት የመደበኛ የደመወዝ ጭማሪ አይሰጥም፡፡

# 3 የደረጃ እድገት

1. ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ውጭ የተገኘና ለቅጥር የተያዘ የሥራ ልምድ ባለሙያው የሙያ ፈቃድ እስካገኝ ለደረጃ እድገት ለምን አያገለግልም? የሥራ ግብር የከፈለበትን ሥራ ልምድ አቅርቦ የተቀጠረ ሠራተኛ ያለሥራ አፈፃፀም ደረጃ ዕድገት መስጠት አይቻልም?

   - የደረጃ ዕድገት የሚሰጠው አንድ የጤና ባለሙያ ተረጋግቶ በመንግሥት መሥሪያ ቤት አገልግሎት እንዲያበረክት ለማድረግ ስለሆነ፣ የደረጃ እድገት ዓላማው በመንግስት ተቋም ለተሰጠ አገልግሎት እውቅና በመስጠት የሚሰጥ የማበረታቻ ክፍያ ነው፡፡ የግል ተቋም ውጤት ተኮር የምዘና ውጤት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ተቀባይነት ስለሌለው የሥራ ልምዱ ለደረጃ እድገት አይያዝም፡፡ ያለ ውጤት ተኮር የምዘና ውጤትም የደረጃ እድገት አይሰጥም፡፡

2. በተመደበበት ደረጃ የመጨረሻ የሥራ ተዋረድ ላይ የደረሰ ወይም ከ10 ዓመት በላይ ያገለገሉ እና በመነሻ ወይም በእርከን ደመወዝ ላይ ያለ ወይም በሀምሌ 2011 ዓ.ም የደመወዝ ሽግግር ወቅት 3 እርከን ተጨምሮለት የነበረ የጤና ባለሙያ ደረጃ ዕድገት ማግኘት ይችላል?

   - በሰለጠነበት ሙያ የመጨረሻ እድገት መሰላል ላይ የደረሰም ሆነ በ2011ዓ.ም የደመወዝ ሽግግር ወቅት ሶስት እርከን የተጨመረለትም ሆነ ሳይጨመር በሙያው የመጨረሻ እድገት መሰላል ላይ የደረሰ የጤና ባለሙያ የትምህርት ደረጃውን አሻሽሎ በሌላ ከፍ ያለ ሙያ ካልተመደበ የደረጃ እድገት ማግኘት አይችልም፡፡

3. በደመወዝ ስኬል ሽግግር ወቅት በነባሩ የደመወዝ ስኬል የመጨረሻ ዕድገት መሰላል ላይ ደርሰው ለነበሩ ወይም መጨረሻው እድገት መሰላለ ላይ ለመድረስ አንድ ደረጃ ቀርቷቸው ለነበሩ ጤና ባለሙያዎች ሶስት እርከን ጭማሪ መስጠቱ ቅሬታ ተፈጥሯል ለምን አስፈለገ? ቀጣይ የደረጃ ዕድገት እንዴት ይሆናል?

➢ ነባር የጤና ተዋረዶች በማጠሩ፣ በነበራቸው ሙያ የመጨረሻ ዕድገት መሰላል ላይ ደርሰው ብዙ ዓመት ያለደረጃ ዕድገት የቆዩ ነባር ሙያተኞችን በአነስተኛ የሥራ ልምድ በተመሳሳይ የመጨረሻ ተዋረድ ላይ ከደረሱ አዲሶቹ ለመለየት ወይም በነባሩ የደመወዝ ስኬል ወደ ቀጣይ የዕድገት መሰላል ላይ አድጋለሁ ብለው ሲጠብቁ አሠራር ለውጡ የመጨረሻው ተዋረድ ላይ የደረሱትን ነባር ሙያተኞችን ከአዲሶቹ ለመለየት የተደረገ ነው፡፡

4. የጤና ደረጃ እድገት መቆያ ጊዜ በፊት ሁለት ዓመት ነበር፡፡ የጤና 3 ዓመት ለምን ሆነ? አሁን ከሌሎች ለየት ባለሁኔታ በየሶስት ዓመት መሆኑ ራሽናሉ ምንድነው?

   ➢ የጤና ሥራ መደቦች የእድገት መሰላል በፊት እስከ ሰባት የሚደርስ የእድገት መሰላል የነበራቸው ሲሆን፣ የመጨረሻው ተዋረድ ላይ ለመድረስ 12 ዓመት ልምድ ይጠይቅ ነበር፡፡ በነጥብ የሥራ ምዘና ከ4 ተዋረድ በላይ ያለው ሥራ ዝርዝር መግለጫ ማዘጋጀት ባለመቻሉ ተዋረዱ አጥሯል፡፡ በዚህ ምክንያት ለጤና የሥራ መደቦች እንደሙያው ደረጃ ከሁለት እስከ አራት የሥራ ተዋረድ ያለው ሥራ ዝርዝር መግለጫ ነው የተዘጋጀው፡፡

   ➢ ከጤና ውጭ ያሉ ሥራ መደቦች ከአራት የሙያ ተዋረዶች በተጨማሪ ቡድን መሪና ዳይሬክተር የሚሉ 6 ያህል ተዋረድ ያላቸው ሲሆን፣ ከ0 እስከ 10 ዓመት ልምድ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ሥራዎቹ ሲመዘኑም ሥራ መደቦቹ እንደሚጠይቁት ልምድ ለምዘና ዋጋ ይሰጣቸዋል፡፡ የጤና ሙያ ተዋረዶች እንደሁኔታው ከ2 እስከ 4 ተዋረድ ብቻ ስላላቸው ለየተዋረዱ የ2 ዓመት ቆይታ ብቻ ቢጠየቅ ኖሮ እጅግ ቢበዛ ከ6 ዓመት በላይ ነጥብ አሰጭ ልምድ አይኖራቸውም ነበር፡፡

   ➢ ይህም ሥራው ሲመዘን ደረጃው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ስለሚኖረው በተዋረዶች መካከል ያለውን ልዩነት በ3 ዓመት ማራራቅ የተሻለ አማራጭ ሆኖ በመገኘቱ እያንዳንዱ ተዋረድ በ3 ዓመት ልምድ

እንዲራራቅ ተደርጓል፡፡ ይህም የሥራ መደቦች ደረጃ አወሳሰን ላይ አዎንታዊ ውጤት አስገኝቷል፡፡

- ለደረጃ እድገት የሶስት ዓመት ቆይታ ጊዜ ያላቸው ጤና ሙያተኞች ብቻ አይደሉም፡፡ የመደበኛ መምህራን የደረጃ እድገት መቆያ ጊዜም 3 ዓመት ነው፡፡

5. የጤና ሙያ ቡድን መሪ እና ዳይሬክተር ለምን የካርየር ዕድገት የለውም? የማበረታቻ እድገታቸው እንዴት ነው የሚፈፀመው?

- የጤና ሥራ አመራር መደቦች ክሊኒካል ኃላፊነት የሌለባቸው፣ ከሌላ ደረቅ ሥራ መደብ ያልተለዩና በውድድር ባለሙያ የሚመደብባቸው የሥራ መደቦች ናቸው፡፡ በሥራው ልዩ ባህርይ ምክንያት የጤና ሥራ አመራር መደቦች ላይ የጤና ሙያተኞች ሲመደቡ የሥራ መደብ የሚጠይቀውን የሥራ ልምድ ማሟላት አይጠበቅባቸውም፡፡ ሙያተኞቹ ባላቸው አነስ ያለ የሥራ ልምድ የሥራ አመራር መደቡን ኃላፊነት በብቃት ሊውጡ እንደሚችሉ መሥሪያ ቤቱ ካመነ፣ የደረሱበትን የጤና ሙያ ደረጃና ደመወዝ እንደያዙ የሥራ አመራር መደቡን ተግባርና ኃላፊነት እንዲያከናውኑ ሊመድባቸው ይችላል፡፡

6. ያልተቆራረጠ ሥራ ልምድ የሚለው ምንድ ነው?

- ያልተቆራረጠ ሥራ ልምድ አንድ የጤና ባለሙያ በሙያው ተከታታይነት ያለውና ምንም ዓይነት ክፍተት ሳይኖረው የሠራበት ልምድ ማለት ነው፡፡

7. ደረጃ እድገት እና ደመወዝ ጭማሪ ሁለቱም ጥር ወይም ሀምሌ ላይ ቢገጥም እንዴት ይሆናል?

- የመደበኛው የደመወዝ ጭማሪ የሚሰጠው ያለፈ አገልግሎት ጊዜን መሠረት አድርጎ ስለሆነ ቅድሚያ መደበኛ የደመወዝ ጭማሪው ከተሰጠ በኋላ በዚያ ላይ የደረጃ እድገት የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ወደፊት

ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ዝርዝር መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ምንም ዓይነት የመደበኛ የደመወዝ ጭማሪ አይሰጥም፡፡

8. መደበኛ ደመወዝ ጭማሪ ሳይክል የደረጃ ዕድገት ማግኛ ጊዜን ይቀይራል?

➢ የደረጃ ዕድገት ቢያንስ የሶስት እርከን ልዩነት ስላለው የእርከን ጭማሪ ኡደት ቆጠራ የደረጃ ዕድገት ከፀደቀበት ጊዜ ቀጥሎ ካለው ጥር ወይም ሀምሌ ጀምሮ ሁለት ዓመት በመቁጠር ስለሆነ፣ ደረጃ ዕድገት የጭማሪ ኡደትን ይቀይራል፡፡ /የመመሪያውን አንቀጽ 10 ይመልከቱ/

9. ሲኦሲ የሌለው ወይም በጤና ሚኒስቴር በላይሰንስ ስር ፈተና ከመጀመሩ በፊት ተመድበው በሥራ ላይ ያሉ የጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ ስለሌላቸው ወደ ደረጃ እድገት ለማስገባት ስለሚያጨቃጭቅ ሙያ ፈቃድ የሌላቸው የጤና ባለሙያዎች ጥር 2013 ዓ.ም የደረጃ ዕድገት ካርየር ማግኛ ጊዜው ቢሆን እንዴት ይስተናገዳል?

➢ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ደረጃ III፣ ደረጃ IV ወይም ደረጃ V ምስክር ወረቀት ይዘው የብቃት ማረጋገጫ ያልነበራቸው የጤና ባለሙያዎች ለመጀመሪያ ድልድል ለአንድ ጊዜ ብቻ ሲኦሲ ሳያመጡ እንዲደለደሉ የተደረገ ቢሆንም፣ በቀጣይ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካላቀረቡ የደረጃ እድገት አይሰጣቸውም፡፡

10. አንድ የጤና ባለሙያ የሙያ ፈቃድ አድሶ ሲመጣ የሚሰጠው የደመወዝ ጥቅም አለ?

➢ የሙያ ፈቃድ አድሶ ማምጣት ብቻውን ምንም ዓይነት የደመወዝ ጥቅም አይስገኝም፡፡

11. አንድ ክሊኒካል ነርስ የትምህርት ደረጃውን በማሻሻል ጥቅምት 2010 ሲንየር ነርስ ፕሮፌሽናል ደመወዝ ብር 5294 ሆኖ ተመድቦ ነበር፡፡ ባለሙያው ሀምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም በተካሄደው የደመወዝ ስኬል ሽግግር በደረጃ XII ነርስ

ኘሮፌሽናል II ሆኖ ሲደለደል ደመወዙ ብር 5886.33 ሆነ፡፡ ባለሙያው በተመደቡበት ደረጃ XII መነሻ ደመወዝ ብር 7071 ላይ ሳይደርስ በጥር 2013 ደረጃ XIII ላይ ሲያድግ የሚደርስበት ደመወዝ በምሳሌ ቢብራራ?

## 11.1 የኊላ ታሪክ

- የደረጃ XII መነሻ ደመወዝ ብር 7017 ነው፡፡
- በሀምሌ 2011 ደመወዝ ስኬል መሸጋገሪያ የደመወዝ ልዩነት በብር 1500 በላይ ሲሆን ልዩነቱ ለሶስት ተካፍሎ በየዓመቱ ደመወዝ ላይ 1/3 ይጨመራል፡፡
- የመሸጋገሪያ ልዩነት

  7017-5294= 1777 / 3 = 592.33

- የመጀመሪያ ዙር ክፍያ ሐምሌ 2011 ደመወዝ/

  5294+592.33= 5886.33

11.2 2ኛ ዙር ክፍያ /ሐምሌ 2012 ደመወዝ/

5886.33+592.33= ብር 6478.66

11.3 የጥር 2013 ደረጃ ዕድገት

- ደረጃ XIII መነሻ ደመወዝ ብር 8017
- የባለሙያው የታህሣሥ 30 ቀን 2013 ደመወዝ ብር 6478.66

  የጤና ባለሙያ ደመወዝ በሁለት ደመወዞች መካከል ካረፈ በቅድሚያ ደመወዙን አቅራቢው ወደ ከፍያለ የእርከን ደመወዝ ላይ ማሳረፍ፡፡

- የባለሙያው ደመወዝ ብር 6478.66 በደመወዝ ስኬሉ በብር 6193 እና ብር 6481 መካከል ላይ ስለሚገኝ ወደ ብር 6481 ከፍ ይደረጋል፡፡ (የነጥብ የሥራ ምዘና ደረጃ አወሳሰን ጥናት የደመወዝ ስኬል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2012 መሠረት አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 8(ለ) ይመልከቱ)፡፡

- ይህ ደመወዝ ከደረጃ XIII ደመወዝ ሲቀነስ ልዩነቱ
  ብር 8017-6481 = ብር 1573 ይሆናል፡፡

- የጥር 2013 ደረጃ ዕድገት በ2ኛ ዙር የደመወዝ ሽግግር ወቅት ውስጥ ስለሆነ የደመወዝ ልዩነቱ ለሁለት ተካፍሎ
  1573 / 2 = 768

- የመጀመሪያ ዙር ክፍያ /የጥር 2013 ደረጃ ዕድገት/
  ይህ የደመወዝ መሸጋገሪያ ልዩነት ታህሳስ 30 ቀን 2013 ዓ.ም ደመወዝ ላይ ሲደመር ብር 6481 + 768 = ብር 7249 ይሆናል፡፡

- 2ኛና የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሐምሌ 2013 ዓ.ም
  7249 + 768 = ብር 8017

12. ታህሣሥ 2013 ዓ.ም ላይ በተመደበበት ደረጃ የመነሻ ደመወዝ በላይ ደመወዝ የሚከፈለው ሠራተኛ ጥር 2013 የደረጃ እድገት ሲሰጠው በምሳሌ ቢብራራ?

ምሳሌ

- ታህሣሥ 30 ቀን 2013 ዓ.ም ላይ አንድ ፋርማሲ ፕሮፌሽናል III፣ ደረጃ XIV፣ 4ኛ እርከን ደመወዝ ብር 10521 ላይ ቢሆን፡-

  - የሚያድግበት ደረጃ XV መነሻ ደመወዝ ብር 10150 ነው፡፡

- የሠራተኛ ደመወዝ ከሚያድግበት የሥራ ደረጃ የመነሻ ወይም የእርከን ደመወዝ ጋር እኩል ወይም በላይ ከሆነ የተመደበበትን ደረጃ የጣሪያ ደመወዝ ሳያልፍ የሶስት እርከን ደመወዝ ጭማሪ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ (የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የሥራ መደቦች ምዘና፣ ደረጃዎች ምደባና ደመወዝ ስኬል ደንብ ቁጥር 455/2011 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2 ይመልከቱ)

➢ ታህሣሥ 30 ቀን 2013 ዓ.ም የጤና ባለሙያው ደመወዝ (ብር 10521) ከሚያድግበት ደረጃ XV የመነሻ ደመወዝ /በብር 10150 / በላይ ስለሆነ በደመወዙ ላይ 3 እርከን ሲጨመር ጥር 1 ቀን 2013 ዓ.ም በደረጃ XV እርከን 4 ብር 11719 ላይ የሚያርፍ ስለሆነ ይህ ደመወዝ ከባለሙያ የታህሣሥ 2013 ደመወዝ ላይ ሲቀነስ ልዩነቱ 11719-10521= 1198 ነው፡፡

- ይህ የደመወዝ ልዩነት ከብር 1500 በታች ስለሆነ በመንግሥት የጤና ተቋማት የሚሠሩ የጤና ባለሙያዎች የቅጥር እና የደረጃ ዕድገት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 4/2013 አንቀጽ 15 መሠረት፡-

- በመጀመሪያ ዙር ክፍያ ብር 1000 ታህሣሥ 30 ቀን 2013 ዓ.ም ደመወዙ ላይ በመደመር በጥር 2013 ደረጃ ዕድገት ደመወዙ

  10521 + 1000 = ብር 11521 ይሆናል፡፡

➢ ሀምሌ 1 ቀን 2013 ቀሪው ብር 198 ሲጨመርለት /11521+198= 11719/ ደመወዙ የሥራ መደቡ ደረጃ XV 4ኛ እርከን ብር 11719 ላይ ያርፋል፡፡

13. ሀምሌ 2010 ዓ.ም የደረጃ ዕድገት ያገኘ ጤና ባለሙያ ከሀምሌ 2010 በኋላ ክርየር ይገባቸው የነበሩና ያላገኙ ባለሙያዎች ሁለቱም 3 ዓመት ስለሚሞላቸው በኋላ የተቀጠረው ይበልጣል እንዴት ይታያል?

➢ ሀምሌ 2010 ዓ.ም የደረጃ ዕድገት ያገኘ ሀምሌ 2013 ዓ.ም ሶስት ዓመት ሲሞላው የደረጃ እድገት የሚያገኝ ሲሆን ከእርሱ በኋላ ተቀጥሮ የደረጃ እድገቱን ከሀምሌ 2010 ዓ.ም በኋላ ጥር 2011 ዓ.ም የደረጃ እድገት የሚያገኝ የጤና ባለሙያ በፊት የተቀጠረውን ባለሙያ የሚበልጥበት ሁኔታ ሊፈጠር አይችልም፡፡

14.ከሀምሌ 2011 ዓ.ም ጀምሮ በተደረገው የጤና ባለሙያዎች ድልድልና በየተመደቡበት የሥራ ደረጃ የመጨረሻ ተዋረድ ላይ ደርሰው የነበሩና ከ10 ዓመት በላይ የሥራ ልምድ የነበራቸው ወይም የተመደቡበት ደረጃ የመጨረሻው ተዋረድ ለመድረስ አንድ ደረጃ የቀራቸውና ከ11 ዓመት በላይ ያገለገሉ 3 እርከን ተጨምሮላቸው የነበረ ሲሆን፣ በወቅቱ ጥቂት ቀናት ወይም ወራት ስለቀራቸው ተጠቃሚ ሳይሆኑ የቀሩ ሠራተኞች አሁን የጐደላቸውን ጊዜ ሲያሟሉ እንደሌሎች ሙያተኞች በደመወዛቸው ላይ ሶስት እርከን ይጨመርልን እያሉ የሚጠይቁ አሉ፡፡ የሚቻል መሆን አለመሆኑ ቢብራራ?

➢ መመሪያው ለአንድ ወቅት ብቻ እንዲያገለግል የወጣ ነው፡፡ ዓላማውም በተመደቡበት ደረጃ የመጨረሻ ተዋረድ ላይ ደርሰው ብዙ ዓመት ያለ ደመወዝ መሻሻል ያገለገሉ እና ወደ አዲሱም ተዋረድ ሲሸጋገሩ በመጨረሻው ተዋረድ IV ላይ ሲመደቡ አዲስ ወደ ተዋረዱ ከሚደለደሉ ሙያተኞች የክፍያ ልዩነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡

15. የJEG ማቺንግ በተሠራበት ወቅት እንደአጻጻፋቸው ቅደም ተከተል 3፣ 6 ወይም 9 ዓመት ለመሙላት ጥቂት ወራት ቀናት ወይም ቀርቷቸው የነበሩ እና በወቅቱ ከተመደቡበት ደረጃ አንድ ደረጃ ከፍ ብለው ለመመደብ ጥቂት ወራት ወይም ቀናት ስለቀራቸው ከፍ ብለው ሳይመደቡ የቀሩ ከድልድሉ በኋላ ሶስት ዓመት ሲሞላቸው ደረጃቸው አለመሻሻሉ የመልካም አስተዳደር ችግር ምንጭ ሆኗል የሚል ቅሬታ ስለሚቀርብ በምን መልኩ ቅሬታቸውን መፍታት ይቻላል? ለቀጣይ የደረጃ እድገት ልምዳቸው እንዴት ይያዛል? ቢብራራ?

➢ የጤና ባለሙያዎች ከነባሩ የደመወዝ ስኬል ወደ አዲሱ የደመወዝ ስኬል ሽግግር የተፈጸመው ባለሙያዎች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የነበራቸውን

የሥራ ልምድ መሠረት በማድረግ ነው። በወቅቱ በየደረጃው ላሉ የጤና ሙያ ተዋረዶች ለመደልደል የነበራቸው 2 ዓመት ከ9 ወር፣ 5 ዓመት ከ10 ወር ወይም 8 ዓመት ከ11 ወር የሥራ ልምድ የነበራቸው ባለሙያዎች እንደአጻጻፋቸው ቅደም-ተከተል 3 ዓመት፣ 6 ዓመት ወይም 9 ዓመት ሲሞላቸው ዝቅ ባለ ደረጃ ላይ የተመደቡ የጤና ባለሙያዎች ከሽግግሩ በኋላ የጐደላቸው ልምድ ሲሞላ ድጋሚ ድልድል ሊፈጸምላቸው አይችልም።

- ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከነባሩ የደመወዝ ስኬል የነጥብ የሥራ ምዘና ሥርዓትን ለመተግበር ወደተዘጋጀው የደመወዝ ስኬል የተሸጋገረው ድልድሉ ሲፈጸም የነበረውን የሥራ ልምድ መሠረት በማድረግ ነው። በ2009 ወይም በ2010 ዓ.ም የሠራተኛ ድልድል በፈጸሙ መሥሪያ ቤቶች የሠራተኞች የሥራ ልምድ የተያዘው ድልድሉ እስከተፈጸመበት ጊዜ ድረስ የነበረ ልምዳቸውን በመውሰድ ነው። በድልድል ወቅት ለቀጣይ የሥራ ተዋረድ ልምድ የጐደላቸው ድልድሉ ከተፈጸመ በኋላ ልምዱ ስለሞላ በቀጣይ የሥራ ተዋረድ ልደልደል ብሎ ጥያቄ ማቅረብ አይችልም።

16. ነሀሴ 2009 ዓ.ም ተቀጥሮ የደረጃ ዕድገት ማግኛ ጊዜው ከመድረሱ በፊት 3 ዓመት ያለፈው ህዳር 2013 ዓ.ም 3 ዓመት ከ4 ወር የሞላው የጤና ባለሙያ ባለበት ተቋም የደረጃ ዕድገት ማግኘት የማይችል ሲሆን፣ 3 ዓመት የሥራ ልምድ ለሚጠይቅ ሥራ መደብ የቅጥር ማስታወቂያ ሲወጣ ሄዶ ይቀጠራል። ለዚህ ሙያተኛ ባባበት ተቋም ጥር 2013 አልደረሰም ብሎ የደረጃ እድገት መከልከሉ ትክክል ነው ወይ?

- የጤና ባለሙያ የደረጃ እድገት ቢያንስ በ3 ዓመት አንዴ በጥር ወይም በሀምሌ ወር መጀመሪያ ላይ ነው። ከሀምሌ እስከ ታህሳስ 30 የተቀጠረ፣ የደረጃ እድገት ያገኘ ወይም የትምህርት ደረጃው በማሻሻል የደረጃ ለውጥ ያደረገ የጤና ባለሙያ የደረጃ እድገት የሚያገኘው ጥር ላይ ነው። ከዚያ በፊት 3 ዓመት ቢያልፈውም ደረጃ እድገት ማግኘት የማይችል ሲሆን

በሙያው ሌላ ተቋም የቅጥር ማስታወቂያ ቢወጣ ግን መቀጠር የሚከለክለው የለም፡፡

17. በትምህርት ላይ የነበሩ የጤና ባለሙያዎች በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት ትምህርት ቤቶች ሲዘጉ ወደ ምድብ ሥራቸው ተመልሰው ያገለገሉ ወይም እያገለገሉ ያሉ ሙያተኞች ልምዳቸው ለደረጃ ዕድገት ይያዛል?

- ለትምህርት ከመሄዳቸው በፊት ለደረጃ ዕድገት የቆይታ ጊዜ ለማሟላት ጥቂት ወራት ወይም ቀናት ቀርቷቸው የነበሩ እና በወረርሽኙ ምክንያት ትምህርት ሲቋረጥ ሀገር ሙያቸውን በከፍተኛ ሁኔታ በምትፈልግበት አስቸጋሪ ሰዓት ወደ ምድብ ሥራቸው ተመልሰው አገልግሎት ያበረከቱ እና እያበረከቱ ያሉ የጤና ባለሙያዎች በፊት ጎድሏቸው የነበረውን ጊዜ የሚያካክስ እና አዲሱ የቆይታ ጊዜ የሞላቸው ለደረጃ ዕድገት ሌሎች ተፈላጊ መስፈርቶችን እስካሟሉ ደረስ የሥራ ልምዳቸው ለደረጃ ዕድገት ይያዝላቸዋል፡፡

18. በዲስፒሊን ጉድለት ከደረጃና ደመወዝ ዝቅ የተደረገ የጤና ባለሙያ ደረጃ ዕድገት አያገኝም የተባለው ምንድነው?

- በከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ምክንያት በጊዜ ገደብ ከደረጃና ደመወዝ ዝቅ እንዲል የተወሰነበት የመንግሥት ሠራተኛ የጊዜ ገደቡን ጨርሶ ወደ ቀድሞ ደረጃና ደመወዙ ይመለሳል፡፡ ሠራተኛ የሚቀጣው ከጥፋቱ እንዲማር ለማድረግ ነው፡፡ ሠራተኞች ከደረጃና ደመወዝ ዝቅ እንደተደረገ ወዲያው በደረጃ በዕድገት ከፍ ወዳለ ደረጃ የሚመለስ ከሆነ ቅጣትን ተርጉም ያሳጣል፡፡ ለሌላውም አስተማሪ አይሆንም፡፡

19. ለደረጃ ዕድገት የሁለት ዓመት ቆይታ ወደ ሶስት ዓመት ሲቀየር በፊት ሀምሌ ላይ የደረጃ ዕድገት ሳይክላቸው የነበረና ጥር 2013 ላይ ከሶስት ዓመት በላይ የሥራ ልምድ ያላቸው የደረጃ ዕድገት በጥር ማግኘት ይችላሉ?

- አይችሉም፡፡ የጤና ባለሙያዎች የደረጃ ዕድገት ማግኛ ጊዜ ከሁለት ዓመት ወደ ሶስት በመቀየሩ  የቀድሞ ቆይታ ጊዜ ላይ የተጨመረው አንድ ዓመት ብቻ በመሆኑ የደረጃ ዕድገት ማግኛ ጊዜያቸው ከሀምሌ ወደ ጥር 2013 አይቀየርም፡፡ ሀምሌ 2011 የደረጃ ዕድገት ያገኙ የጤና ባለሙያዎች ሶስት ዓመት የሚሞላቸው ሀምሌ 2013 ላይ ነው፡፡

- ሆኖም የመጀመሪያ የደረጃ ዕድገት ሳያገኙ ሶስት ዓመት ያለፋቸው ከሀምሌ 2009 እስከ ታህሣሥ 2010 የተቀጠሩ ወይም የትምህርት ማሻሻያ አቅርበው የደረጃ ለውጥ ያደረጉ ሙያተኞች ጥር 2013 ላይ የደረጃ ዕድገት የሚያገኙ ይሆናሉ፡፡

20. ከመጋቢት 2009 ዓ.ም በፊት የተቀጠሩ የጤና ባለሙያዎች ደረጃ ዕድገት ሁኔታ ግልጽ ቢደረግ?

- ከጥር 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2009 ዓ.ም የተቀጠረ ወይም የደረጃ እድገት ያገኘ ወይም የትምህርት ማሻሻያ በማቅረብ የደረጃ ለውጥ ያደረገ የጤና ባለሙያ ሀምሌ 2011 ዓ.ም የደረጃ እድገት አግኝቷል፡፡

21. ከጥር 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የደረጃ ዕድገት የሚያገኙት መቼ ላይ አድገው የነበሩ ናቸው?

- ጥር 2010 ዓ.ም የደረጃ እድገት ያገኙ፣ የጤና ባለሙያዎች  ወይም ከሀምሌ 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2010 ዓ.ም ተቀጠሩ ወይም የትምህርት ደረጃቸውን አሻሽለው የደረጃ ለውጥ ያደረጉ ጥር 2013 ዓ.ም ሶስት ዓመት ስለሚሞላቸው ከጥር 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የደረጃ እድገት የሚያገኙ ይሆናል፡፡

ይገዙ ጅማነህ አ...
የተቀማጭ አደ/ዳ/ሪ...
የሲቪ ሰ/ሰ/ዳ/ጀ/...

## 4 ትምህርት ማሻሻያ

1. ከ10 ዓመት በላይ ልምድ ያለው የጤና ባለሙያ ከሚያገለግልበት ተቋም ለትምህርት ተልኮ የትምህርት ደረጃውን አሻሽሎ ሲመለስ በመመሪያው አንቀጽ 9.2 መሠረት በትይዩ ደረጃ አመዳደብ እና ቀጣይ የደረጃ ዕድገት አሰጣጥ በምሳሌ ቢብራራ?

   - አንድ የጤና ባለሙያ ለትምህርት ከመሄዱ በፊት 10 ዓመት አገልግሎት ከነበረው በነባር ሙያው የመጨረሻ እድገት መሰላል ላይ ስለሚደርስ ሲመለስ በአዲሱ ትምህርት ቀድሞ ይዞት ከነበረው ደረጃ ትይዩ በሆነ ደረጃ ላይ ይመደባል፡፡

**ምሳሌ** ደረጃ 4 ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኒሺያን III ደረጃ XI ወይም ቴክኒሺያን IV ደረጃ XII ላይ የነበረ የጤና የባለሙያ የትምህርት ደረጃውን አሻሽሎ ሲመለስ **ደመወዙ ሳይነካ** በነበረበት ደረጃ XI ወይም ደረጃ XII ላይ ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኖሎጂ ፕሮፌሽናል ሆኖ ይመደባል፡፡

### የትይዩ ደረጃ አመዳደብ ናሙና

| ደረጃ | የደረጃ 4 ዕድገት መሰላል | የመጀመሪያ ዲግሪ የዕድገት መሰላል | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| IX | ደረጃ 4 ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኒሺያን I | | |
| X | ደረጃ 4 ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኒሺያን II | | |
| XI | ደረጃ 4 ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኒሺያን III | ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኖሎጂ ፕሮፌሽናል I | ትይዩ |
| XII | ደረጃ 4 ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኒሺያን IV | ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኖሎጂ ፕሮፌሽናል II | ትይዩ |
| XIII | | ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኖሎጂ ፕሮፌሽናል III | |
| XIV | | ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኖሎጂ ፕሮፌሽናል IV | |

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

- ለትምህርት ከመላኩ በፊት ደረጃ XI ላይ ደርሶ የነበረ የደረጃ 4 ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኒሽያን III ትምህርቱን ጨርሶ ሲመለስ በቀድሞ ደረጃው ትይዩ ሚዲካል ላቦራቶሪ ቴክኖሎጂ ፕሮፌሽናል I ደረጃ XI ላይ የሚመደብ ሲሆን፣ በዚህ መደብ ላይ ከተመደበበት ጊዜ ጀምሮ የደረጃ ዕድገት ዑደቱን ጠብቆ በየሶስት ዓመቱ ደረጃ XII፣ XIII እና XIV ላይ ያድጋል፡፡

- ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኒሻያን IV ደረጃ XII ላይ ደርሶ የነበረ ባለሙያ ትምህርቱን ጨርሶ ሲመለስ በቀድሞ ደረጃው ትይዩ በሆነው ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኖሎጂ ፕሮፌሽናል II ደረጃ XII ላይ የሚመደብ ሲሆን ወቅቱን ጠብቆ ሶስት ዓመት ሲሞላው ቀጣይ ደረጃ ዕድገቱን ያገኛል፡፡

2. የትምህርት ደረጃውን አሻሽሎ የተመለሰ የጤና ባለሙያ በትምህርት ላይ ያሳለፈው ጊዜ እንደ ሥራ ልምድ ስለማይያዝ ሲመለስ ከአቻ ጓዶቹ በደመወዝ ስለሚያንስ የገንዘብ ጥቅም አያገኝም ከተባለ የቅሬታ መንስኤ አይሆንም?
   - አንድ ሠራተኛ ለትምህርት ማሻሻያ የሚላከው ለሠራተኛው ጥቅም ለማስገኘት ብቻ ሳይሆን፣ ትምህርቱ ለሥራው አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ነው፡፡ ደመወዝ የሚከፈለው ባለሙያ ለሚያከናውነው ሥራ እንጂ ሙያተኛው ያለውን የትምህርት ዝግጅት ታሳቢ በማድረግ አይደለም፡፡ ይህን ባለሙያው ለትምህርት ከመላኩ በፊት በቅድሚያ ተረድቶ ሊስማማበት ይገባል፡፡

   - ትምህርት እንደጥቅም ማግኛ ከታየ በአዲሱ የሥራ ምዘና ሥርዓት በየደረጃው ያሉ ሙያተኞች ሙያቸውን ባሻሻሉ ቁጥር በነባር የትምህርት ደረጃቸው ሊደርሱባቸው የማይችሉ ከፍ ያለ ተጨማሪ የደረጃ ዕድገት መሰላሎች ያስገኙላቸዋል፡፡

   **ለምሳሌ፡-** የደረጃ 4 ባለሙያዎች የዕድገት መሰላል ጣሪያው ደረጃ XII ነው፡፡ አንድ የጤና ባለሙያ፣ ትምህርቱን በመጀመሪያ ዲግሪ ሲያሻሽል እስከ ደረጃ XIV ወይም ደረጃ XV ከዚያም ትምህርቱን ወደ ሁለተኛ ዲግሪ ሲያሻሽል እስከ ደረጃ XVI ወይም እስከ ደረጃ XVII የዕድገት መሰላሎች ያሉት ደረጃዎች ይጠብቁታል፣ እንዲህ እያለ እስከ ደረጃ XXII ይደርሳል፡፡ ይህ

በትምህርት ማሻሻል ሠራተኛው የሚያገኘው ጥቅም መሆኑን ለጤና ባለሙያዎች ማስገንዘብ ይገባል፡፡

3. ሙያ ማሻሻያ የሚያደርግ ጤና ሙያተኛ ከነባር ትምህርት ደረጃው እንደሁኔታው አራት ወይም ሁለት ዓመት ሲያዝ ሲንየር ወይም ችፍ ተብሎ ይመደብ ነበር፡፡ አሁን ሲቀር ቅሬታ አያስነሳም?

- በነባሩ የሥራ ምዘና ሥርዓት ከአምስት እስከ ሰባት የሥራ ተዋረድ የነበራቸው የጤና ሥራ መደቦች በነጥብ የሥራ ምዘና ተዋረዳቸው ከሁለት እስከ አራት የሥራ ተዋረድ ሆኗል፡፡ ነባር የትምህርት ደረጃውን ያሻሻለ ባለሙያ እንደቀድሞው አራት ዓመት ወይም ሁለት ዓመት የሥራ ልምድ ተይዞለት ይመደብ ቢባል በተለይ ሁለት ወይም ሶስት ተዋረድ ብቻ ያላቸው ስፔሻሊስቶች በአንድ ጊዜ የመጨረሻ ተዋረድ ላይ እንዲደርሱ ስለሚያደርግ የጤና ሙያተኞች በሰለጠኑበት ሙያ በቂ አገልግሎት እንዳይሰጡ የሚገድብ ስለሆነ በነባር የትምህርት ደረጃ የተገኘ ልምድን መያዝ የሚቻል አልሆነም፡፡

4. በፊት በነበረው አሠራር የጤና ባለሙያ ከትምህርት ሲመለስ የእርከን ማስተካከያ ይደረግለት ነበር አሁንስ?

- አንድ የጤና ባለሙያ እንደማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ትምህርት አሻሽሎ ስለተመለሰ ብቻ የሚደረግለት የደመወዝ ማሻሻያ አልነበረም፡፡ ወደፊትም አይኖርም፡፡ ሆኖም ባለሙያው ያሻሻለው ሙያ የመጀመሪያ የዕድገት መሰላል ለትምህርት ከመሄዱ በፊት ከነበረበት ደረጃ ከፍ ያለ ከሆነ በአዲሱ ሙያ የመጀመሪያ የዕድገት መሰላል ላይ ተመድቦ እንዲሠራ ይደረጋል፡፡

5. ከጤና ሙያ ውጭ የተደረጉ የቀድሞ ጤና ሙያተኞች Msc ሠርተው ሲመለሱ የቀድሞ ልምዳቸው ይያዝልን እያሉ ስለሆነ ምን እናርግ? ወይም ቀደም ሲል በSociology, Biology, Rural Development የሙያ ፈቃድ አግኝቶ በኬርየር የሚተዳደር ባለሙያ በነጥብ የሥራ ምዘና ባለመመዘኑ ከሙያ መስመር የወጣ ሆኖ በመሀሉ MPH ማስተርሱን አጠናቆ ሲመለስ ባልተመዘነ የሙያ መስመር እያገለገለ

የቆየ አገልግሎት ይያዛል ወይስ በማስተርሱ መነሻ ደረጃ XIII ብቻ ይሰጠዋል? ለምን? በመሀል ቅሬታ በዝቷል፡፡ ባልተመዘኑ የሙያ ዘርፍ ውጪ በሆኑ የተሰጠ አገልግሎት ለአንድ ጊዜ አራት ዓመት አገልግሎት ተይዞ ማስተርሶች ደረጃ XIV እንዲያገኙ ተደርጎ የነበረው አሠራር አሁን ተሽሮ ከሆነ ማብራሪያ ቢሰጥ?

- Msc በጤና ሙያ ከሆነ ሁለተኛ ዲግሪ በሚጠይቁ የፕሮፌሽናል ስፔሻሊስት የሥራ መደብ የመጀመሪያ ተዋረድ ላይ ልምዳቸው ሳይያዝ ይመደባሉ፡፡

6. ሙያቸውን ያሻሻሉ ሠራተኞች ደረጃ ዕድገት አሰጣጥ እንዴት ይሆናል?

- በግላቸው ትምህርታቸውን የሚያሻሽሉ ሠራተኞች በተቋሙ ውስጥ ክፍት ሥራ መደብ ካለና ተቋሙ የሥራ መደቡ በሠራተኛ እንዲሞላለት የሚፈልግ ከሆነ ሊደለደሉ ይችላሉ፤ ሆኖም ተቋሙ በግላቸው ተምረው የሚመጡ ሠራተኞችን የመደልደል ግዴታ የለበትም፡፡

7. “ተቀባይነት ባለው ምክንያት” ትምህርት አቋርጦ የተመለሰ የጤና ባለሙያ በፊት በነበረበት ደረጃ ይመደባል የተባለው ተቀባይነት ያለው ምክንያት የሚለው ምን ምን ናቸው ተቀባይነት ያላቸው ምክንያቶች በምሳሌ ቢብራራ?

- ተቀባይነት ያለው ምክንያት የሚለው የባለሙያውን ሁኔታ ወይም የሚያቀርበውን ምክንያት አሳማኝነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በተቋሙ የሚወሰነው ነው፡፡

  **ለምሳሌ፡-** ትምህርቱን ለመከታተል የማያስችል ህመም፣ ተጠርጥሮ በህግ ቁጥጥር ስር መዋል፣ ቤተሰብን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ሁኔታ መፈጠር፣ በትራንስፖርት መታገድ ምክንያት የምዝገባ ጊዜ ማለፍ የመሳሰሉ ሁኔታዎችን ሊያካትት ይችላል፡፡

8. ከመጀመሪያ ትምህርታቸው ወጣ ብለው አዲስ ሙያ ተምረው የሚመጡ ጤና ሙያተኞች የበፊት ሥራ ልምዳቸውን አለመያዙ ቅሬታ እየፈጠረ ስለሆነ እንዴት ይታያል?

- አዲስ የተማሩት ሙያ ከመጀመሪያ ትምህርታቸው ጋር ተያያዥነት ከሌለው ልምዱ አይያዝም፤ በአዲሱ ሙያ የመጀመሪያ ተዋረድ ላይ ይመደባሉ፡፡

9. ከሐምሌ 2012 ዓ.ም በኋላ ከክሊኒካል ነርስ ወደ ኘሮፌሽናል ትምህርት ማሻሻያ ያደረገ የጤና ባለሙያ ያገኘው የደመወዝ መሸጋገሪያ ልዩነት ከብር 1500.00 በላይ ከሆነ ለ2 ተካፍሎ ነው ወይ የሚከፈለው?

   - ከሐምሌ 2012 ዓ.ም በኋላ የሚሰጥ የደረጃ እድገት ልዩነት ከብር 1500.00 በላይ ከሆነ ይህን ልዩነት ለ2 በማካፈል ውጤቱን ባለሙያ ደመወዝ ላይ ተደምሮ ይከፈለዋል፡፡ (ዝርዝር ምሳሌውን ጥያቄ ቁጥር 10 ንዑስ ቁጥር (10.3) ላይ ይመልከቱ)

10. ከዲኘሎማ ወደ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ያሻሻለ የጤና ባለሙያ አንዳንድ የፌዴራል እንዲሁም የክልሎች እና ዩኒቨርስቲዎች 4 ዓመት በቀድሞ ትምህርት ዝግጅት የሥራ ልምድ ያላቸውን ቀጥታ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ካስቀመጠው የክፍያ መመሪያ ውጭ ደረጃ XII መነሻ ደመወዝ ብር 7071.00 በአንድ ጊዜ በመክፈል ልዩነት በመፈጠሩ ቅሬታ እያስነሳ ስለሚገኝ ለወደፊት ወጥ የሆነ አሠራር እንዲፈጠር ምን መደረግ ይኖርበታል?

    - አዲስ የወጣው መመሪያ እና ወደ ሥራ ሲገባ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ማብራሪያ በጽሁፍ ጭምር ተዘጋጅቶ እንዲተላለፍ የተደረገው አንድ ወጥ አሠራር በሁሉም ተቋም እንዲኖር ለመደገፍ ነው፡፡

## 5 ልዩ ልዩ

1. ከጤና ሙያ ውጭ የተደረጉ ረዳቶች ከ15 ዓመት በላይ የሥራ ልምድ እያላቸው ደረጃ X ላይ እንደወሰኑ መደረጉ አገልግሎታቸውን ጥቅም ያሳጣል፣ ሙያተኞቹንም ከሥራ ውጭ ያደርጋል። መደቦቹ ወደፊት ለምን ይጠፋሉ ተባለ?

    - የጤና የአገልግሎት አሰጣጥን ደረጃ ከፍ ለማድረግ ታስቦ ሙያዎቹ ከጤና ካሪኩለም ውጭ የተደረጉ ናቸው የስልጠና ፕሮግራሞቹ ከተቋረጡ ብዙ ዓመት አልፏቸዋል። የሙያተኞችን ደረጃ ለማሻሻል ብዙ ጥረት ቢደረግም ሊሳካላቸው ያልቻሉ ጥቂት ሠራተኞች በዘርፉ ስላሉ የእነርሱን አገልግሎት በጊዜያዊነት ለማስቀጠል የተፈጠሩ የመሸጋገሪያ መደቦች ናቸው።

2. የጤና ሥራ ዝርዝር አልደረሰንም፣ ጥያቄ ከሠራተኞች እየቀረበ ነው ምን ታስቧል?

    - የሥራ ዝርዝር መግለጫዎች የማጥራት ሥራ እንደተጠናቀቀ ለሁሉም ይላካል።

3. ብዙ ዓመታት ሠርተው ልምድ ያካበቱ ሙያተኞችን 6 ወይም 9 ዓመት ልምድ በሚጠይቅ የሥራ መደብ ላይ እንዲመደቡ ማድረግ 15 ዓመት እና በላይ የሥራ ልምድ ያለውን ጤና ባለሙያ ዋጋ የሚያሳጣ ቅሬታ የሚፈጥር ስለሆነ እንዴት ይታያል?

    - የሥራ ደረጃ የሚሰጠው ሠራተኛ ላለው ልምድ ሳይሆን ሥራው ለሚያወጣው ዋጋ ነው። በነጥብ የምዘና ሥርዓቱ የሥራ መደቦች የሚጠይቁት ከፍተኛው የሥራ ልምድ 10 ዓመት ነው። ከዚያ በላይ ያለው የሥራ ልምድ የትኛውም የሥራ መደብ የማይፈልገው ስለሆነ ዋጋ አይሰጠውም።

4. ከድጋፍ ሰጪ ማስተርስ እና ፒ.ኤች ዲ ያላቸው የሚነሳ ጥያቄ ነው። ቀደም ሲል የደረጃ እድገት ሲወጣ ዲግሪ የሥራ ልምድ 6 ዓመት ቢጠይቅ በማስተርስ ደግሞ 4

ዓመት ይጠይቅ ነበር። ነገር ግን አሁን በJEG ማስተርስና ፒ.ኤች.ዲ ጥናቱ ውስጥ ያልተካተተበት ምክንያት ቢገለጽልን።

➢ ድጋፍ ሰጪ ሥራ መደቦች ሆነው ማስተርስ ወይም ፒ.ኤች.ዲ ትምህርት የሚጠይቁ የሥራ መደቦች አሉ። በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ የሥራ መደቦች ከሚመዘኑባቸው መስፈርቶች መካከል ትምህርት ዝግጅት አንዱ ነው። ለእያንዳንዱ መስፈርት የሚሰጥ ነጥብ ያለ ሲሆን፣ እያንዳንዱ የሥራ መደብ የሚመዘነው በአንድ የትምህርት ደረጃና በአንድ የሥራ ልምድ ብቻ ነው። ሥራው የሚጠይቀው አንድ ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ብቻ ነው ለምዘና ጥቅም ላይ የሚውለው። ሥራው የመጀመሪያ ዲግሪና 4 ዓመት ልምድ የሚጠይቅ ከሆነ 2ኛ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ አግባብ ያለው የትምህርት ደረጃ እስካሟላ ድረስ ሥራው የሚጠይቀው ልምድ (4 ዓመት) አይቀንስለትም፤ እንደቀድሞው ከፍ ያለ ትምህርት ሥራ ልምድን የመካካስ የምንዛሪ አሠራር የለም።

5. ለ6 ዓመታት ያለማቋረጥ በመንግሥት መስሪያ ቤት ሲሠራ ምንም ዓይነት ደረጃ ዕድገት ያልተሰጠውና የሙያ ፈቃድ ያለው የጤና ባለሙያ ከመቼ ጀምሮ የደረጃ ዕድገት ይሰጠዋል?

➢ አንድ የጤና ባለሙያ 6 ዓመት በመንግሥት መስሪያ ቤት ካገለገለ ቢያንስ ለ2 ጊዜ ያህል የደረጃ እድገት ማግኘት ነበረበት፡-

- የዲሲፕሊን ጉድለት ወይም የሥራ አፈጻጸም ወይም የተመደበበት ደረጃ የመጨረሻ እድገት መሰላል ላይ በመድረሱ ወይም በሌላ ህጋዊ በሆነ ምክንት የደረጃ እድገት ሳያገኝ በተለያየ ምክንያት ሳያገኝ የቆየ የጤና ባለሙያ ከሀምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ በተደረገው የደመወዝ ስኬል ሽግግር በአዲስ የሙያ እድገት መሳላሉ የመጨረሻ የእድገት መሰላሉ ላይ ካልደረሰ ጥር 2013 ዓ.ም የደረጃ እድገት ማግኘት ይችላል።

6. ለትምህርት የሄደ የጤና ባለሙያ ትምህርቱን አሻሽሎ ሲመለስ ይዞት የነበረውን የመደብ መታወቂያ ቁጥር ይዞ ነው የሚቀጥለው ወይስ ኮንቨርሽን ይሠራለታል ወይስ ተምሮ በመጣው ትምህርት ሌላ መደብ ማስፈቀድ አለብን?

➢ ለአንድ የትምህርት ደረጃ የተፈቀደ የመደብ መታወቂያ ቁጥር ለሌላ ሙያ አያገለግልም፡፡ በመስሪያ ቤቱ የተፈቀደለት የትምህርት ደረጃውን አሻሽሎ የተመሰለ ባለሙያ በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ባለ ክፍት መደብ ወይም ከሌለ አዲስ የሥራ መደብ በማስፈቀድ ሊመደብ ይገባል፡፡

7. በጥር 2012 በስህተት የደረጃ ዕድገት የተሰጣቸው የጤና ባለሙያዎች በጥር 2013 የደረጃ እድገት ከሚያገኙ ጓደኞቻቸው ጋር ሲነጻጸር ተጐድተናልና በ2012 የተከፈለንን መልሰን ከጥር 2013 ጀምሮ የደረጃ ዕድገት ይሠራልን እያሉ የሚጠይቁ ባለሙያዎችን እንዴት እናስተናግድ?

➢ በ2 ዓመት አንድ ጊዜ ይከፈል የነበረው የጤና ባለሙያዎች የደረጃ እድገት ከሀምሌ 2011 ዓ.ም በኋላ በየ3 ዓመት እንዲሆን በመደረጉ በጥር 2012 ዓ.ም እና በሀምሌ 2012 ዓ.ም የጤና ባለሙያዎች የደረጃ እድገት እንደማይኖር በወቅቱ መመሪያ መውጣቱ ይታወቃል፡፡ መመሪያውን በመተላለፍ የደረጀ እድገት ተሰጥቷቸው የነበሩ የጤና ባሙያዎች በፈቃዳቸው ወደ ትክክለኛው መስመር ለመግባት ያለአግባብ ተከፍሏቸው የነበረውን ደመወዝ ለመመለስ ፈቃደኛ ከሆኑ የሚበረታታ ነው፡፡

8. በየመስሪያ ቤቱ ላሉ የጤና ባለሙያዎች የሚተላለፈው ባለአራት ተዋረድ የእድገት መሰላል በተመሳሳይ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ግልጽ መመሪያ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ለሁሉም መስሪያ ቤቶች ቢተላለፍ?

➢ ታህሳስ 23 ቀን 2013 ዓ.ም በቁጥር ሲ/ሰ/ኮ/30/ጠ10/6/13 የተላለፈው በመንግስት የጤና ተቋማት የሚሠሩ የጤና ባለሙያዎች የቅጥርና የደረጃ እድገት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 4/2013 ሙሉ ምላሽ ለመስጠት ነው፡፡

9. የጤና ባለሙያዎች ለተቋሙ በተፈቀዱ በሥራ አመራር መደቦች ላይ ዕድገት በማግኘት መሥራት እንደሚችሉ ነው፡፡ ነገር ግን በሥራ አመራር መደብ ላይ የተመደቡ ወደ ጤና ባለሙያ የሥራ መደብ ላይ መመለስ ይችላሉ ወይ?

- የደረሱበትን የሙያ ስያሜና ደረጃ እንደያዙ የጤና ሥራ አመራር መደቦች ላይ ተመድበው የሚያገለግሉ የጤና ባለሙያዎች በሚፈልጉ ጊዜ ወደ መደበኛ ሙያቸው ተመልሰው ክሊኒካል አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ሲሆን፣ በሥራ አመራር መደብ ላይ ያበረከቱት አገልግሎት ለደረጃ እድገት ይያዝላቸዋል፡፡ ሆኖም ከሌሎች ሙያተኞች ጋር ተወዳድሮ በጤና ሥራ አመራር መደብ ላይ የተመደበ የጤና ሥራ አመራር ባለሙያ ተመልሶ ወደነባር ሙያ መሰላል አይመለስም፡፡

ይገዙ ጀማነህ ኪሮስ
የተቋማዊ አደ/የሥራ ሃ
የሰው ሃ/ል/ዳይ/ዳ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

# ማብራሪያው የተላከላቸው መ/ቤቶች ዝርዝር

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቶች ስም ዝርዝር በስያሜ | አድራሻ |
|---|---|---|
| 1. | ለሰላም ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 2. | ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 3. | ለገንዘብ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 4. | ለግብርና ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 5. | ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 6. | ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 7. | ለትራንስፖርት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 8. | ለከተማ ልማት ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 9. | ለውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 10. | ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 11. | ለትምህርት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 12. | ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 13. | ለጤና ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 14. | ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 15. | ለሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 16. | ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 17. | ለሰብአዊ መብት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 18. | ለፌዴራል የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 19. | ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 20. | ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 21. | ለአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 22. | ለሥራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 23. | ለብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 24. | ለመስኖ ልማት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 25. | ለውሃ ልማት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 26. | ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 27. | ለስፖርት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 28. | ለፕላንና ልማት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 29. | ለዕርቀ ሰላም ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 30. | የአስተዳደር ጉዳዮች፣ የወሰንና ማንነት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 31. | ለብሮድካስት ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 32. | ለቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 33. | ለእንስሳት መድሃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 34. | ለፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪግ ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 35. | ለንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 36. | ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 37. | ለኢትዮጵያ ጨረራ መከላከል ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 38. | ለኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን | አዲስ አበባ |

| | | |
|---|---|---|
| 39. | ለፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 40. | ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 41. | ለኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 42. | ለተፋሰሶች ልማት ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 43. | ለኢትዮጵያ ኢነርጅ ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 44. | ለኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 45. | ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 46. | ለኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 47. | የነዳጅ የነዳጅ ውጤቶችና አቅርቦት ስርጭት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 48. | ለፌዴራል ከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 49. | ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 50. | ለመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 51. | ለኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 52. | ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 53. | ለመንግሥት  ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 54. | ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች  ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 55. | ለሠነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 56. | ለህብረት ሥራ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 57. | ለኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 58. | ለመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 59. | ለፌዴራል ከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 60. | ለፌዴራል ለተቀናጀ መሠረተ ልማት ማስተባበሪያ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 61. | ለብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 62. | ለሀገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 63. | ለከፍተኛ ትምህርት አግባቡነትና ጥራት ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 64. | ለግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 65. | ለስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 66. | ለብሔራዊ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻህፍት ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 67. | ለማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 68. | ለፌዴራል ቴክኒክና ትምህርት  ሙያ ስልጠና ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 69. | ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 70. | ለፕሬዚዳንት ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 71. | ለህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 72. | ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 73. | ለኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 74. | ለመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 75. | የውሀ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 76. | ፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 77. | ለፌዴሬሽን ምክር ቤት | አዲስ አበባ |
| 78. | ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት | አዲስ አበባ |
| 79. | ለጠቅላይ  ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 80. | ለከፍተኛ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |

| | | |
|---|---|---|
| 81. | ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 82. | ለጠቅላይ ሸሪያ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 83. | ለኢትዮጵያ ከይዘን ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 84. | ለስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 85. | ለውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 86. | ለፍትህና የሕግ ምርምርና ስልጠና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 87. | ለኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 88. | ለብሔራዊ እንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 89. | ለብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 90. | ለጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 91. | ለቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 92. | ለብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 93. | ለምግብ፣ የመጠጥና የፋርማሲቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 94. | ለኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 95. | ለስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | ደብረዘይት |
| 96. | ለኢትዮጵያ ብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 97. | ለኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 98. | ለኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 99. | ለቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 100. | ለጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 101. | ለኮንስትራክሽን ሥራዎች ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 102. | ለውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 103. | ለፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 104. | ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 105. | የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 106. | ለፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 107. | ለኢትዮጵያ ብዝሃ-ህይወት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 108. | ለኢትዮጵያ አካባቢና ደን ምርምር ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 109. | የኢትዮጵያ የአፈር ሀብት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 110. | ለፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 111. | ለብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርምርና ጥናት ማዕከል | ሰበታ |
| 112. | ለኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማት ማስፋፊያ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 113. | ለከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂክ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 114. | ለሆቴሎችና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 115. | ለአትሌት ጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 116. | ለገፈርሳ የአዕምሮ ህሙማን ማገገሚያ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 117. | የህገመንግስትና ፌዴራሊዝም አስተምህሮ ማእከል | አዲስ አበባ |
| 118. | ለቤተ መንግሥት አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 119. | ለብሔራዊ ሎቶሪ አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 120. | ለሚዛን የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ | ሚዛን |
| 121. | ለአጋርፋ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ | አጋርፋ |
| 122. | ለአላጌ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ | አላጌ |

| | | |
|---|---|---|
| 123. | ለአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ | አርዳይታ |
| 124. | ለገዋኔ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ | ገዋኔ |
| 125. | ለሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ | አዲስ አበባ |
| 126. | ለአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ | አዲስ አበባ |
| 127. | ለአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ | አዳማ |
| 128. | ለድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ | ድሬዳዋ |
| 129. | ለደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ | ደብረብርሃን |
| 130. | ለሰመራ ዩኒቨርስቲ | ሰመራ |
| 131. | ለደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ | ደብረማርቆስ |
| 132. | ለአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ | አርባ ምንጭ |
| 133. | ለወሎ ዩኒቨርሲቲ | ደሴ |
| 134. | ለመቱ ዩኒቨርሲቲ | መቱ |
| 135. | ለአዲግራት ዩኒቨርሲቲ | አዲግራት |
| 136. | ለአሶሳ ዩኒቨርሲቲ | አሶሳ |
| 137. | ለወልዲያ ዩኒቨርሲቲ | ወልዲያ |
| 138. | ለደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ | ደብረ ታቦር |
| 139. | ለጋምቤላ ዩኒቨርስቲ | ጋምቤላ |
| 140. | ለቦንጋ ዩኒቨርስቲ | ቦንጋ |
| 141. | ለመቅደላ ዩኒቨርስቲ | ቱሉ አወሊያ |
| 142. | ለደባርቅ ዩኒቨርስቲ | ደባርቅ |
| 143. | ለደንቢዶሎ ዩኒቨርስቲ | ደንቢዶሎ |
| 144. | ለእንጅባራ ዩኒቨርስቲ | እንጅባራ |
| 145. | ለኦዳቡልቱም ዩኒቨርስቲ | ጭሮ |
| 146. | ለሰላሌ ዩኒቨርስቲ | ሰላሌ |
| 147. | ለራያ ዩኒቨርስቲ | ራያ |
| 148. | ለጂንካ ዩኒቨርስቲ | ጂንካ |
| 149. | ለቀብሪደሀር ዩኒቨርስቲ | ቀብሪደሃር |
| 150. | ለቦረና ዩኒቨርስቲ | ቦረና |
| 151. | ለመለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ | አዲስ አበባ |
| 152. | ለኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ | አዲስ አበባ |
| 153. | ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ | አዲስ አበባ |
| 154. | ለኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ | አዲስ አበባ |
| 155. | ለመንግሥት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 156. | ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር | አዲስ አበባ |
| 157. | ለህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም | አዲስ አበባ |
| 158. | ለቱሪዝም ኢትዮጵያ | አዲስ አበባ |
| 159. | ለኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ | አዲስ አበባ |
| 160. | ለግብርና ምርምር ካውንስል ሴክሬታሪያት | አዲስ አበባ |
| 161. | ለጠቅላይ ዓቃቤ ህግ | አዲስ አበባ |
| 162. | ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ | አዲስ አበባ |
| 163. | ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት | አዲስ አበባ |
| 164. | የሪፐብሊኩ ጥበቃ ኃይል | አዲስ አበባ |

Civil Service Commission

ይገዛ ቸማህ ...
የተቀማጥ ...

| ተራ ቁጥር | የመሥሪያ ቤቶች ስም ዝርዝር በስያሜ | አድራሻ |
|---|---|---|
| 1. | ለኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና መልካም አስተዳደር ቢሮ | አዲስ አበባ |
| 2. | ለአማራ ብ/ክ/መንግስት ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | ባህርዳር |
| 3. | ለደቡብ ብ/ብ/ህ/ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ሀዋሳ |
| 4. | ለትግራይ ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | መቐሌ |
| 5. | ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | አዲስ አበባ |
| 6. | ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ድሬዳዋ |
| 7. | ለሐረሪ ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ሐረሪ |
| 8. | ለሶማሌ ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ጅግጅጋ |
| 9. | ለአፋር ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ሰመራ |
| 10. | ለጋምቤላ ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ጋምቤላ |
| 11. | ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | አሶሳ |
| 12. | ለሲዳማ ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ሀዋሳ |

ይገዙ ጀማነህ
የተቋማዊ አደ/የሥራ
የሰው ሃ/ል/ዳይ/